በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ተፈጥሮ ለነበረው ብጥብጥ መፍትሔ የሰጠበት ጽሑፍ አንደኛው ነው:: በጊዜው የብጥብጡ መንሥኤ መሪዎችን ለሁለት በመለየት አሮጌው ትውልድና አዲሱ ትውልድ የሚል እንቅስቃሴ መከሰት ነበር:: የዚህ የልዩነቱ መንሥኤ በዕድሜ መግፋትና ወጣትነት ነበር:: በወቅቱ ወጣቶች በመሪነት ላይ ያሉት አይመጥኑንም በማለት አውርደው ብጤዎቻቸውን ተክተዋል:: ይህ ደግሞ የጉባኤውን የመንፈስ አንድነት አጥፍቶ ንትርክ እና ልዩነትን አነገሠ:: በዚህ ወቅት የሮሙ ቀለሚንጦስ በተከታዩ ደብዳቤው መልእክቱን አደረሰ:-

> «እግዚአብሔር ያደረጀውን ሥርዓት መጠበቅ ብቸኛ መፍትሔ ነው:: እግዚአብሔር የደኅንነት ዕቅዱን እንኳን የገለጸው ሰንሰለታዊ በሆነ የተዋረድ አካሄድ ነው:: እግዚአብሔር አብ ኢየሱስ ክርስቶስን ላከ፣ ክርስቶስ ሐዋርያትን ላከ፣ ሐዋርያት መጋቢዎችንና ዲያቆናትን መረጡ፣ እነርሱ ደግሞ ቀጣዮቻቸውን ሾሙ:: ይህ አካሄድ ተገቢ እና ትክክል ነው:: ቤተ ክርስቲያን መሪዎቿን ከዚህ ውጪ ብታስተናግድ፣ ትጠፋለች:: ከዚህም የተነሣ፣ ያዋረዳችኋቸውን ወደ ቦታቸው በመመለስ አክብሩአቸው::»

ይህም የነበረውን ሁከት አስተካክሏል:: ይህ መልእክት በየዘመኑ የተነሡትን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ክፍፍል ለመግታት አቅም እንደ ነበረው ማስተዋል ይቻላል::

**የአንጾኪያው ኢግናጢየስ** (Ignatius of Antioch):-ኢግናጢየስ በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን 2ኛው ክፍለ ዘመን መነሻ ላይ በመጋቢነት ያገለግል ነበር:: ይህ ሰው ክርስቲያን ከመሆኑ የተነሣ በወታደሮች ተይዞ ወደ ሮም በ110 ዓ.ም. ተወስዶ ተገደለ:: ኢግናጢየስ ወደ ሮም እየተጓዘ ሳለ ሰባት ደብዳቤዎችን ለመጻፍ ችሏል:: በኤፌሶን ላሉ ቤተ ክርስቲያናት፣ ለፊላደልፊያ፣ ለትራሊስ፣ ማግኒዥያ፣ ለሰምርኔስ፣ ለሮም ቤተ ክርስቲያናት፣ በተጨማሪም ለመጋቢው ፖሊካርፕ የግል ደብዳቤ ጽፎ ነበር::

ኢግናጢየስ በጻፋቸው ደብዳቤዎች በአብዛኞቹ የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ ጉዳይ «አንድነቷን መጠበቋ ነው፣



እያንዳንዱ አጥቢያም አንድ መጋቢ ብቻ ሊኖረው ይገባል» በማለት ሲጽፍ፣ በሁሉም መልእክቶቹ የክርስቶስን ትምህርት መግለጽ እና ስለ ክርስቶስ መሥዋዕት ለመሆን መዘጋጀት የክርስቲያን ሁሉ ኑሮ መሆኑን ከመከረ በኋላ፣ የእርሱም ፍጻሜ ስለ ጌታው መሥዋዕት መሆን እንዳለበት የሚገልጽ መልእክትን ጽፏል::

**ዲዲስቅልያ** (The Diadache):- ዲዲስቅልያ በአንደኛውና በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ላይ እንደ መመሪያ በመሆን አጥቢያዎቹን ያገለገለ መጽሐፍ ነው:: መጽሐፉ በ100 ዓ.ም. ላይ ከሶሪያ ምናልባትም ከአንጾኪያ የተገኘ ነው:: የመጽሐፉ ዐቢይ ርእሰ ጉዳይ «ለአሕዛብ የጌታ ትምህርት በ12ቱ ሐዋርያት አማካኝነት» የሚል ነው:: በውስጡ የያዛቸው ርእሰ ጉዳዮች ለሁለት ተከፍለዋል፤ ክፍል አንዱ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ላይ በማተኮር፣ የሕይወት መንገድ እና የሞት መንገድ በሚሉ ንዑስ ርእሶች ተከፍሏል፤ ክፍል ሁለቱ ደግሞ፣ ቤተ ክርስቲያናት ጸሎትን፣ ጾምን፣ ጥምቀትን፣ የጌታ ራትን፣ የቤተ ክርስቲያን አመራርን፣ ነቢያትንም (መልእክተኞችን) እንዴት ማስተናገድ እንደሚገባቸው ይዘረዝራል::

**የፍርጊያው ፓፒየስ** (The Phrygia of Papius):- ይህ ሰው (110-30 ዓ.ም.) በታናሿ እስያ በምትገኘው በፍርግያ መጋቢ ሆኖ አገልግሏል፤ በወንጌላት ያልተመዘገቡትን የኢየሱስ ትምህርቶችን በማሰባሰብ ይታወቃል፤ ስብስቡን ከኢየሩሳሌም ውጭ ሆነው ካሉት የአይሁድ ክርስቲያኖች የተቀበለው ነው:: እነርሱ ከኢየሩሳሌም ከመውጣታቸው በፊት ያዩትንና ያደመጡትን ሁሉ ከእነርሱ ወስዶ ጽፏል:: ብዙዎች ፓፒየስ ያሰባሰባቸውን ጽሑፎች ከኢየሱስ እና ከሐዋርያት ትምህርት ጋር አይጣጣሙም በማለት አልተቀበሏቸውም፣ የተቀበሏቸውም ደግሞ አሉ:: የተቀበሏቸው መነሻ፣ «ኢየሱስ ያደረገው ቢጻፍ ዓለም አይበቃውም» የሚለው ቃል ነው (ዮሐንስ 21)::

**በእስክንድርያ የተጻፈው የበርናባስ መልእክት** (Epistle of Barnabas):- የተጻፈው 120 ዓ.ም. ገደማ ነበር:: ጽሑፉ «የብሉይ ኪዳን ጽሑፎች በክርስቲያናዊ መንገድ እንዴት ለአገልግሎት

የሮማውያን ትምህርት ቤቶች ዐቢይ ትምህርታቸው ባህላዊውንና ንጉሣዊውንም አምልኮን የማራመድ ሥርዓትን ማስተማር ነበር::

በተያያዥ፣ የሙያ ዘርፎች ሁሉ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለሮማውያን ሕዝባዊ እምነት መገለጫ በመሆን ስለ ደረጁ፣ ክርስቲያን የሆነ ባለሙያ በተዘዋዋሪ ክርስቶስን የሚቃወም ሥራን ሊሠራ ስለሚችል፣ ብዙዎች ሥራቸውን ትተዋል::

ጠብደሎች በሚያካሂዷቸው የቡጢ እና የትግል ሜዳም እስመገኘትን ክርስቶስ ሰዎች ይጋደሉ ዘንድ ሳይሆን፣ በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ይወዳል በማለት ድርጊቱንም ሆነ ትርዒቱን ይቃወማሉ::

ክርስቲያኖች ሮም በምታስተዳድረው አገር ሁሉ የተስፋፋውን በማኅፀን ያለን ፅንስ እንዲሁም፣ እንደ ተወለደ የሚፈጸምን ውርጃና ግድያ፣ እንዲሁም ልቅ ፍቺ ይቃወሙ ጀመር::

እነዚህ ሁሉ ተጠቃልለው፣ በሮማውያን ዘንድ ክርስቲያን ማለት፣ «አብሮ የመኖር ጠላት፣ ራሳቸውን ከልክ በላይ ያከፈሉ ጻድቃን፣» ተብለው ለሮም ሥርዓት እንቅፋት ተደርገው ተፈረጁ::

# ምዕራፍ ስድስት

## በነገሥታት የተመራ ስደት

ክርስቲያኖች ላይ ስደትን በማነሣሣት ቀዳሚው ንጉሥ ኔሮ ነበር:: ይህ ንጉሥ ከተማዋን እቃጥሎ ክርስቲያኖች ናቸው ብሎ ሲያውጅ፣ ላሰበበት በቂ ምክንያት አዘጋጅቶ ነበር:: እነዚህ በቂ ምክንያቶች ክርስቲያኖች ኅብረተሰቡ ውስጥ ሲኖሩ ይወስዷቸው የነበሩትን አቋሞች ግምት ውስጥ መክተት ዋንኛው ነበር::

ተርቱሊያን በተከታታይ ተካሂደው የነበሩትን ስደቶች ሲያስረዳ፣ «በክርስቲያኖች ላይ ስደትን ያስነሡ ክፉ የሮማ መሪዎች ቢኖሩም፣ ስደትን ባለማካሄድ በክርስቲያኖች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያደርሱ የነበሩ የሮማ ንጉሦች ነበሩ:: . . .» ኔሮ (54-68)፣ እና ዶሚሺያን (81-96) ክርስቲያኖችን በአረመኔያዊ መንገድ



ጨፈጨፉ፣ እንደ ኮምዶስ (180-92) ያሉት ደግሞ ክፉ መሪ ዎች ናቸው፤ ቢሆንም ግን፣ በክርስቲያኖች ላይ ታጋሽነትን አሳዩ፤ እንደ ትራጃን (98-117) የመሰሉ ደግ መሪዎች፣ እንደ ማርከስ አውሩለስ (161-80) የመሰሉ ፈላስፋ መሪዎች ደግሞ በክርስቲያኖች ላይ በተዘዋዋሪ ስደትን ቀሰቀሱ::

ለስደት መንሥኤ ከሆኑት ዋንኛ አጀንዳዎች ውስጥ፣ «እውነተኛው እምነት እና የመዳኛ መንገድ በእኛ ዘንድ ይገኛል፣» ማለታቸው ቀዳሚው ነበር:: በሮም ግዛቶች ሁሉ ያሉ ሃይማኖቶች፣ «እኔ ብቸኛ መፍትሔ ለሰኝ፣ ወይም እኛን እመኑ፣» አያሉም:: እያንዳንዱ ሮማዊ ሁሉንም ሃይማኖቶች ቀይጦ መኖር ይችላል:: ክርስቲያኖች ግን ክርስቶስን ብቻ የመዳን ጎዳና፣ ሌላው ሁሉ የጥፋት እምነት መሆኑን እያበሰሩ በማርዳታቸው ተወገዙ::

አይሁዳውያን በሮማውያን ዘንድ ተወዳጅ የሆኑት፣ እምነታቸውን ቢያስፋፉ የሚደርሱት አይሁዶችን ብቻ ነው፣ አሕዛብን ወደ ይሁዲ እምነት እንዲመጡ እያስገድዱም:: ክርስቲያኖች ግን እንዲህ አልነበሩም፤ አይሁዳዊ፣ አረመኔያዊ አይሉም፣ ይህ ጥላቻን ፈጥሮ ስደትን አመጣ::

ንጉሡ ነገሥቱን ስማምለክ ፈቃደኛ አለመሆናቸው ሌላኛው የስደት መንሥኤ ነበር:: ንጉሡን ማምለክ ለመንግሥቱ ታማኝነትን መግለጽ ነበር፤ የትኛውም ዜጋ ክርስቲያን መሆን አለመሆኑ የሚፈተሸው ለቆመው የንጉሥ ምስል ጸሎትና መሥዋዕት በማድረስ «ቄሳር ጌታ ነው» ብሎ ሲመሰክር ነበር:: ክርስቲያኖች፣ «ኢየሱስ ጌታ ነው» የሚል ጽኑ እምነት ነበራቸው::

በተያያዥ፣ አረማውያን (Pagans) ክርስቲያኖችን የብልሹ ሥነ ምግባር መንሥኤዎች በማድረግ ያሳድዷቸው ነበር:: ከምክንያቶቻቸው ጥቂቶቹ፣ ሰው በላነት (በላኤ ሰብ) የሚል ነበር:: ለዚህ የተዛባ ግንዛቤ የጌታ ራትን የመውሰድ ሥርዓታቸው አንዱ ነበር፣ «የክርስቶስን ሥጋ እንበላለን፣ ደሙን እንጠጣለን፣» የሚለውን አባባል፣ «ሰው-በላ» በማለት ስማቸውን አጠፉ:: «ወንድም እና እኅት» በሚል ስም የመዳራትና የፍትወት መገለጫቸው ነው በሚል ከሰሉዋቸው::

ለእነርሱ ተብሎ ሌላ የቅጣት ደንብ መውጣት አይገባውም፤ ባለው ሕገ-ደንብ መሠረት ይተዳደሩ፣» የሚል ምላሽን ጻፈለት። በዚህ ዘመን ውስጥ ክርስቲያን በመሆን ብቻ ያለ ምክንያት የሚሆነው ቅጣት ረገብ አለ።

4) በሀድሪያን የስደት ዓመታት (Hadrian, 117-138):- ሀድሪያን የትራጃንን ፖሊሲ ተከትሏል። ሕዝቡ በዐመፀኝነት ተነሣሥቶ፣ «ለንጉሡና ለአማልክት ክብር የማይሰጡት የክርስቲያኖች ደም ዛሬ ይፍሰስ» እያሉ ሲጮሁ፣ ንጉሡ የሰጠው መመሪያ:-

1. ያለበቂ ምክንያት ክርስቲያኖች አይሳደዱም።
2. ተከስሰው በቀረቡ ጊዜ ስለ ራሳቸው የመከላከል መብት አላቸው።
3. በክርስቲያኖች ላይ በሐሰት ክስ የመሠረቱ ይቀጣሉ።
4. ክርስቲያኖች በክሳቸው ምላሻቸው ከአገሪቱ ሕገ-ደንብ ጋር ከተጣረሰ፣ ሊቀጡ ይገባል፤ የሚል ነበር።

ይህም ደንብ በዐመፅ ተነሣሺነት በግብተኝነት ከሚያጠፋቸው ታደጋቸው፤ ክርስቲያን በመባላቸው ብቻ የመጣባቸው ቅጣት ቀረላቸው፤ እንደዚያም ቢሆን፣ ከንጉሣዊ አምልኮ ጋር ባለመተባበራቸው ምሕረትን አጡ።

5) በአንቶኒዮስ ፒዩስ የስደት ዓመታት (Antonius Pius. 138-161):- የትራጃንን እና የሀድሪያንን መንገድ ይህ ሰው አልተከተለም፤ ሕዝብ በዐመፅ ተነሣሥቶ ለሚፈጽመው ግብታዊ ጥፋት ምላሽ ሳይሰጥ ዝም አለ። ሕዝቡ፣ «መናፍቃኑ አማልክትን የናቁ ስለሆኑ፣ ቁጣ መጣብን» በሚል ሰበብ ክርስቲያኖች አለቁ። በ155 ዓ.ም. ፖሊካርፕ በሕዝብ ዐመፅ በእሳት ከመንደዱ በፊት ጌታውን እንዲክድ በተጠየቀ ጊዜ፣ «ለ86 ዓመታት አንዴም አላስከፋኝም፤ እንዴት ጌታዬንና አዳኜን ዛሬ አሳዝነዋለሁ . . .» ነበር ያለው።

6) በማርቆስ አውሬልዩስ የስደት ዓመታት (Marcus Aurelius, 161-180):- ይህ ሰው ወደ ሥልጣን የወጣው ፋርስ በሮም ላይ ጦርነት በከፈተችበት ወቅት ነበር። መጠነ ሰፊ ረሀብ እና የምድር



ነውጥ ተከስቶ ስለ ነበር፣ ሕዝቡ «ክርስቲያኖችን መንግሥት በመታገሡ የአማልክት ቁጣ እያደገ መምጣቱን በመግለጽ ዐመፀ።» ንጉሡ በጦርነቱ በመሸነፉ፣ እንዲሁም የተከሰተውን ተፈጥሮአዊ ጥፋት መግታት ባለመቻሉ፣ የሕዝቡን ድምፅ እንደ አማልክቱ ድምፅ ቆጠረ። በክርስትና ታሪክ ወደር የሌለው መጠነ ሰፊ ስደት በእርሱ ዘመን ተከፈተ።

7) በኮሞዶስ የስደት ዓመታት (Commodous, 180-192):- የማርቆስ ልጅ የሆነው ኮሞዶስ፣ የአባቱን ፈለግ በመከተል ስደቱን አሳደገ። ይህ ሰው 300 ቅምጦች ነበሩት፤ ከእነርሱ አንዷ በንጉሡ ፊት፣ «በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው ስደት ተገቢ አለመሆኑን» ከማስረዳቷ የተነሣ፣ ስደቱን ለተከታታይ 20 ዓመታት እንዲቆም ያደረገ ንጉሥ ነበር።

## የየዘመኑ የእምነት ዐቃብያን

ከ2ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ *ሀ)* የባህላዊ እምነት ተከታዮች፣ *ለ)* በግሪክ አስተሳሰብ በመንዛት ፍልስፍናን እንደ እምነት የተረዱ ሰዎች፣ እንዲሁም *ሐ)* ጭፍን የሆኑ የክርስትና ተቃዋሚዎችን ለመግታት፣ ለመርታት እና የክርስትናን መሠረታዊ እምነት ለመግለጽ፣ በየዘመኑ በርካታ ጸሐፊዎች ተነሡ። እነዚህ ሰዎች ዐቃቤ እምነት (አፖሎጂስት) በመባል ተጠሩ።

በጊዜው የነበሩት የእምነት መከላከያ መግለጫዎች፣ መቶ በመቶ ማለት ይቻላል፣ የተጻፉት በግሪክ ቋንቋ ነበር። ይህ ጽሑፍ ለሚመለከታቸው ተቃዋሚዎች፣ በተለይ በየጊዜው በተለያየ መንገድ ስደትን ለሚቀሰቅሱ እና ለማይገቱ የሮማ ነገሥታት እና አስተዳዳሪዎች የሚላክ ነበር። ጽሑፎቹ በይዘታቸው፣ ክርስቲያኖች ሕግን አክባሪ፣ ለመንግሥታቸው ተገቢውን ግብር ከፋዮች፣ የበጐ ሥነ ምግባር ባለቤቶች መሆናቸውን ከመግለጽ ባሻገር፣ የክርስትናን በላጭ እምነትነት ያስረዱ ነበር። እነዚህ ከዐቃቤ እምነት የተፈረጁ ሰዎች «ተራ ሰዎች» አልነበሩም፤ ብዙዎቹ ክርስቲያን ከመሆናቸው በፊት፣ ስለ ፍልስፍና በቂ ዕውቀትን ያከማቹና የታሪክን ጉዞ በመረዳት ትላንትን ከዛሬ፣ ዛሬን ከነገ ማስተሳሰር የሚችሉ ነበሩ።

ግሪካውያን የፍልስፍናቸው አቅጣጫ ከአመክንዮ ወይም ቅቡል ከሆነ ሕገ ደንብ አኳያ ያዘሰቀው ራሱ ነው በማለት ዘርዝሯል::

የፕሌቶ አስተማሪ ስለ ነበረው አርስጣጣሊስ ሲናገርም፣ «ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱ በፊት ክርስቲያን የነበረ ፈላስፋ» በማለት ይጠራዋል:: ይህን ሲልም፣ ክርስትና የግሪክ ፍልስፍና ሙልዐት ነው በማለት ነው:: ከዚህም የተነሣ፣ ፍልስፍና ከክርስትና ጋር ተጋጪና ተጣይ ሳይሆን፣ ሊቀራረቡና ሊቀባበሉ የሚችሉ የትምህርቶች ክምችት ነው:: ፈላስፎች የሁሉ ነገር ትርጓሜን ገነጣጥለው በቱናጠል አጠኑዋቸው፤ ክርስትና ግን ሙሉ ምስሉን አኖረ::

ጀስቲን «ቃለ ምልልስ» በማለት በሚጠራው ጽሑፉም፣ ክርስትና ፀረ-ይሁዲ እምነት አይደለም፤ ይልቅስ፣ የይሁዲነትና የብሉይ ኪዳን መደምደሚያ ነው በማለት ከአይሁዶች ጋር መቀራረብን ለማምጣት የጣረ ሰው ነበር::

በሰማዕትነት በ165 የተገደለው ጀስቲንም ሆነ ሌሎች ዐቃብያን ጽሑፎቻቸውን ለነገሥታቱ ቢጽፉም፣ የማናቸውም በመሪዎቹ አልተነበቡም፤ ባይነበቡም፣ ጽሑፎቹ የክርስቲያኖችን እምነት አጸኑ፤ ለሰማዕትነትም አዘጋጁ::

# ምዕራፍ ሰባት

## የአፍሪካ ክርስትና - አሌክሳንደሪያ እና ካርቴጅ

ሮማውያን አፍሪካ ብለው ሲሰይሙ የሚሉት የሰሜን ምዕራብ እና ምሥራቅ አፍሪካን ብቻ ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ይህ ክልል ቱኒዚያን፣ አልጄሪያን፣ ሞሮኮን፣ ሊቢያንና ግብፅን ሸፍኖ የሚገኘው ነው:: ከእነዚህ አምስቱ ሁለቱ፣ አሌክሳንደሪያ ከሰሜን ምሥራቅ፣ ካርቴጅ ከሰሜን ምዕራብ ባሉት ከተሞች ላይ ከፍተኛ መናኸሪያ በመሆን ከሮም ቀጥለው ያሉ ሁለት ከተሞች ሆነው ተቆጥረዋል::

***1. ቤተ ክርስቲያን በእስክንድርያ:-*** *የእስክንድርያው* ቀለሚጦስና ኦሪገን እንዳሉት፣ እስክንድርያ የጥበብ እና የሥልጣኔ



ማዕከል ሆና ትታወቃለች፣ በንግዱ ዓለም ወደቦቿ ያለ ዕረፍት የሮምን ግዛቶች ያገለግሉ ነበር፣ የግሪክና የሮም አስተሳሰብና ሥልጣኔ የሰፈነበት በመሆኗ የቅይጥ ኅብረተሰብ ባለቤት ነበረች፤ በርካታ አይሁዶች ይኖሩባት የነበረ መሆኑ ደግሞ በተጨማሪ ያለውን የአመለካከት ስፋት አግዝፎታል::

ክርስትና በዚህ አገር እንዴት እንደ ተስፋፋ የሚታወቅ የጎላ ፍንጭ የለም፤ ተነሺ መረጃ ይኑረን ከተባለ ሐዋርያት ሥራ 18:24 -28 ያለው ገለጻ አጋዥ ይሆናል::

> «. . . በወገኑም የእስክንድርያ ሰው የሆነ ነገር አዋቂ የነበረ አጵሎስ የሚሉት አንድ አይሁዳዊ ሰው ወደ ኤፌሶን ወረደ፤ እርሱም በመጻሕፍት እውቀት የበረታ ነበረ:: እርሱ የጌታን መንገድ የተማረ ነበረ . . . ስለ ኢየሱስ ይናገርና በትክክል ያስተምር ነበር:: እርሱም በምኵራብ ገልጦ ይናገር ጀመር:: ጵርስቅላና አቂላም በሰሙት ጊዜ፣ ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በትክክል ገለጡለት::»

በአይሁድ ክርስቲያኖች ዘንድ በየምኵራቡ የወንጌል ትምህርት ተስፋፍቶ እንደ ነበረ በዚህ መገንዘብ ይቻላል::

**የእስክንድርያው ቀለሚንጦስ:-** (በ215 ዓ.ም አረፈ) ታላቅ የክርስትና መምህር ነበር:: ሞክሼው ቀለሚንጦስ በሮም ስላለ ለመለየት የእስክንድርያው ቀለሚንጦስ ብሎ መጥራት አስፈለገ:: ይህ ሰው ዳግም ከተወለደ በኋላ ከበርካታ የክርስትና መምህራን እውቀትን ለመገብየት በየአገሩ ዞሯል:: ከእስክንድርያ የተገኘው ይህ ሰው በሦስት የተመደቡ በርካታ ጽሑፎችን ጽፏል:-

ምድብ 1. ግሪካውያንን-ደራሽ ጽሑፎች:- በጽሑፎቹ የአረማውያንን አማልክት እየተቸ፣ የእነርሱ ተከታዮች ወደ ክርስቶስ ዘወር ይሉ ዘንድ ያመለክትበታል:: ሰዎች ሁሉ አይሁድ ቢሆኑ አረማውያን ያለ ክርስቶስ ትምህርት የሙሉ እውቀት ባለቤት አይሆኑም በማለት ጽፏል::

ምድብ 2. ሰዳግም ተወላጆች አዳዲስ አማንያን ክርስትናን እንዴት ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚያብራራ መጽሐፍ ነው:: በዓለም

ውስጥ እንዴት ሊኖሩ እንደሚገባ፣ በምግብ፣ በመጠጥ፣ በመስተንግዶ፣ በጋብቻ፣ በመዝናኛ፣ በሙዚቃ እና በመሳሰሉት ሁሉ ላይ ገለጻ አድርጓል። ጭምቅ መልእክቱ፣ «ኑሮ:- መናጢ በመሆን ወይም ቅንጦት የሞላው ሀብታም ከመሆን ላይ ሳይሆን፣ ለኑሮ የሚያስፈልገንን ብቻ እንዲኖረን በሚያግዝ አኗኗር እንኑር» ይላል።

ምድብ 3. ዘርፌ-ብዙ:- በርካታ ርእስ ጉዳዮችን በመቀያየጥ የጻፈበት መጽሐፍ ነው። ብዙው የየግል ገጠመኞቹንና ልምዶቹን አስፍሮበታል።

**ኦሪገን (185-254)**:- በ185 ዓ.ም. ከክርስቲያን ቤተሰቦቹ የተወለደው ኦሪገን የእስክንድርያ ሰው ነበር። ይህ ሰው የቀለሚንጦስ ተማሪ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት እና የግሪክ ፍልስፍናን በመርመር የታወቀ ነበር።

በኦሪገን ላይ ከሚነገሩት ጉዳዮች አንዱ ሰማቴዎስ 19:12 የነበረው መረዳት ቀጥተኛ መሆን ነበር። «በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፤ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፤ ስለ መንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦችም አሉ።» ይህን ገለጻ ኦሪገን በገዛ ሕይወቱ ላይ ተፈጻሚ አድርጎታል።

ኦሪገን በዕድገቱ ውስጥ ባገኘው ግንዛቤ ድርጊቱ አግባብ እንዳልሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነው። ይህ ሰው ቅዱሳን መጻሕፍትን የሚተረጉምበት የሥነ አፈታት ስልት አለው። ንባባትን በሦስት ደረጃ በመከፈል ወደ ትክክለኛ መረዳት መምጣት ይቻላል ይላል።

ንባብ 1 Body (አካል)- የሚለው- የቃል በቃል ልሙጥ ፍቺ ነው።

ንባብ 2 Soul (ነፍስ) - የሚለው - የሞራላዊ ሥነ ምግባራዊ ፍቺን ነው።

ንባብ 3 Spirit (መንፈስ) የሚለው- የመንፈሳዊ (ጥልቅ) ትርጉምን ነው።



ይህም ሰው የሦስት ቅንጅት ባለቤት ሆኖ ሳለ፣ «አንድ ሰው» እንደሚባል ሁሉ፣ ቅዱሳን መጻሕፍትም አንድ ግብ ቢኖራቸውም፣ በየፈርጃቸው ማጤን ተገቢ ነው ይላል። ይህም ከፍፍሉ ግልጽ (ስም) እና ስውር (ወርቅ) ፍቺን በመያዙ፣ አጥኚ ሁሉ ስስውሩ መገዛት አለበት ይላል።

የኦሪገንን አጠናን በሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል:-

«ሦስት አባቶች ለልጆቻቸው ምግብ አዘጋጁላቸው፣» በሚለው ንባብ ውስጥ የቃል በቃል ፍቺው፣ «3 ወንድ ወላጆች ልጆቻቸው የሚመገቡትን ምግብ አዘጋጁ» ማለት ነው። ስውሩ መንፈሳዊው ግን ሦስቱ ሥላሴን ይወክላል፣ ምግቡ የጌታን ራት ያመለክታል፤ ልጆቹ አማንያንን በማመልከቱ፣ ተፈላጊው ምሥጢር «አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ያድጉ ዘንድ የጌታን ራት አዘጋጁላቸው» የሚል ይሆናል።

ኦሪገን ቃል በቃል የሆነውንና ሥነ ምግባራዊ ትርጓሜን ሳይተው ነው ይህን በምሥጢራዊነት በመደበል ቅድሚያ የሚሰጠው። ኦሪገን እንዲህ የመተርጎም ስልት ከግሪክ የፍልስፍና መሠረት ከሆኑት ከሆሜር የኢሊያድ (Iliad) እና ኦዲሴ (Adyssey) የግጥም ድርሳናት የአተረጓጎም መሠረትን ሳይጠቀም አልቀረም። ከቀጥተኛ ፍቻቸው ባሻገር ትርጓሜያቸውን የመተንተንና ምሥጢርን የማውጣት ሥራም ነበራቸው።

**2. ቤተ ክርስቲያን በካርቴጅ - ተርቱሊያን እና ሳይፕሪያን:**
- በሰሜን ምዕራብ አፍሪካ ባሉት ክልሎች ያሉ ሕዝቦች ቅይጥ ናቸው። ፊንቂያውያንና ፍልስጥኤማውያን፣ የጢሮስና የሲዶና ሰዎች በአገሪቱ ዳርቻዎች ላይ መጥተው በመኖር ከነዋሪዎቹ ጋር ተቀላቅለዋል፣ የደቡብ ስፔን ሰዎችም ተቀይጠዋቸዋል። ሕዝቡም ለምዕራባውያኑ ባህልም ተጋልጧል። በዚያ ክርስትና እንዴት እንደ ተጀመረ መተንተን አይቻልም። በ180 ዓ.ም. ገደማ ግን 12 ክርስቲያኖች በሰማዕትነት እንደ ተገደሉ ተጽፏል። ይህ በአሁኗ ቱኒዚያ የተከናወነ ነበር። ይህ ደግሞ በሮማውያን ከተቀሰቀሱት ስደቶች ጋር ተያያዥነቱን ያመለክታል።

እክብሮት በመስጠት ለተለያዩ ክስተቶች አማልክትን ለይመዋል:: ለፀሐይም የነበራቸውን ግንዛቤ በማስፋት የሁሉ ነገር ማዕከል ፀሐይ መሆኗን ይገልጻሉ:: ይህ አመኔታ ያድግ ዘንድ በ274 ዓ.ም. በሮም ታላቅ ቤተ መቅደስ ለፀሐይ ማምለኪያ በንጉሡ ትእዛዝ ተሠራ::

የፀሐይን ልደት ለማክበርም ዲሴምበር 25 ተመረጠ:: የምሥራቃውያንን እምነት የሚያስተናግዱት የሮም ወታደሮችም «የብርሀን አምላክ»ን ይታመኑበት ስለ ነበር፣ አዲሱ የፀሐይ አምልኮ ከጦር ኃይሉ ጋር ተስፋፊ ሆነ:: በፀሐይ በኩል አንድ አምላክን መረዳት ይቻላል የሚለው ይህ እምነት ብዙ ክርስቲያኖች «ልዩነቱ አልታየንም» በማለት አምልኮውን ይለማመዱት እንደ ነበር ይታወቃል::

2. ኒዎፕላቶኒዝም (Neoplatonism):- ፕሎቲነስ (Plotinus, 205-70) በሮም የተማረ ግብፃዊ ሰው ነበር:: የግንዛቤው መሠረት የፕሌቶ (Plato) አስተምህሮ ነበር:: ፍልስፍናው «በመሰላል» ይመሰላል:: ከላይኛው ተርታ ካለው የመጀመሪያ ርብራብ ላይ እግርን ማሳረፍ ማለት ወደ ትክክለኛው የተፈጥሮ እና የገዛ ማንነት መገለጫ ላይ መገኘት ነው ካለ በኋላ፣ እርሱን ተከትሎ ያለው ርብራብ ላይ አግርን ማሳረፍ በእእምሮ ይመሰላል፤ እንደ የእግዚአብሔር ልጅ የእግዚአብሔር መገለጫ ተብሎ ታምኗል:: ይህ አእምሮ ዛሬ ያለውን ፍጥረት ወደ ሕልውና አምጥቷልም፤ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሦስተኛው ርብራብ ነፍስ ነው፤ ይህም በእእምሮና ባለው ቁሳዊ ዓለም መካከል ያለ ክልል ነው:: የሰው እእምሮና ነፍስ በዚህ መሥመር ላይ ይቀራረባሉ:: ከዚህ ቀጥሎ ያለው (አራተኛው) ርብራብ ቁሳዊው ዓለም ነው፤ እንግዲህ ሰዎች ሁሉ በከፍተኛ ሥነ ሥርዓታዊ አኗኗር ወደ ጫፉ ለመድረስ መጣር አለባቸው:: ይህ እምነት (361-3) ሮምን ያስተዳደረው ጣልያኖስ ከሃዲው (Julian the Apostate) ይታመንበት ስለ ነበር ክርስቲያኖችን ይጠላ፣ ያሳድድም ነበር:: ኒዎፕላቶኒዝም ከክርስትና ትምህርት የወጣ፣ በተግባሩ የቤተ ክርስቲያን እሳዳጅ ሆኖ ዘልቋል::



**3. ማኒኬይዚም** (Manichaeism):- ይህ **እንቅስቃሴ** ከኖስቲሲዝም (Gnosticism) አስተሳሰብ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው:: መሥራቹ ማኒ (Mani, 216-77) ይባላል:: እርሱ ሰው ራሱን «የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ነኝ» ብሏል:: ከዚህም የተነሣ፣ ቀድሞ የነበሩት ሃይማኖቶች እና ፍልስፍናዎች ሙሉ አይደሉም፣ ለሙላታቸው «አዲስ መገለጥን ተቀብያለሁ» ባይ ነው::

ማኒ የዓለምን ምንነት ለማብራራት ብርሀንና ጨለማ በሚያደርጉት ፍልሚያ የሚመጣው የበላይነት ሁሉን ነገር አቅጣጫ ያስይዛል ይላል:: ሰዎች በገዛ ራሳቸው ውስጥ የጨለማንና የብርሃንን አቅጣጫ ያራምዳሉ:: እያንዳንዱ ጨለማን ለማሸነፍና ለመውጣት የሚያደርገው ጥረት ራሱን ወደ ፍጹምነት ያመጣለታል:: ለዚህም አጋዥ የሆኑ ሁሉ ተባባሪ ሆነው ለጦርነቱ ውጤታማነት እገዛን ያደርጋሉ:: ከአጋገሮቹም:- ቡድሀ (Buddha) የቡድሃ እምነት መሥራች እና ትምህርቱ:: ዞሮአስተር (Zoroaster) የዞሮአስቶር እምነት መሥራች እና ትምህርቱ:: ኢየሱስ (Jesus) የክርስትና እምነት መሥራች እና ትምህርቱ:: ማኒ (Mani) የማኒኬይዝም እምነት መሥራች እና ትምህርቱ ሁሉ ላይ የሚገኙቱን ቁም ነገሮች ማዋሃድ ተገቢ ነው::

የማኒ ፍልስፍና ቁሳዊውን ዓለም እንደ ርኩስ አድርጎ በመቁጠር፣ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ባለመቀበል ከኖስቲስዝም (Gnostics) ጋር ያመሳስለዋል::

ማኒ ትምህርቱ ብስለት ያለውና ለግንዛቤ ምቹ መሆኑን በማረጋገጥ ተከታዮቹን ለሁለት ይከፍላቸዋል፤ እነርሱም ምርጦች ለሚዎች እና ምርጦች ጠንካሮች ሲሆኑ፣ ለሚዎቹ ግን ለተግባር ደካሞች ናቸው::

በዘመኑ እነዚህ ሦስት ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች በክርስትናና በቤተ ክርስቲያን ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አድርገዋል::

11. ዶናተስ (Donatus) የዳርፔጅ መጋቢ እና መለሎች ከክርስቲያናዊ ፈለግ የወጡትን በመቃወማቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነርሱን ማሳደድ መጀመር።
12. በምዕራቡ የሮማ ግዛት ጳጳሱ ከንጉሡ የበለጠ ኃይል ሲኖረው፣ በምሥራቁ ንጉሡ ከጳጳሱ የገዘፈ ሥልጣን ማግኘቱ።

ለ12ኛው ተነሺ ነጥብ ማብራሪያ እነሆ:-

በምሥራቁ የኮንስታንቲኖፕሉ ዮሐንስ (347-407) በመባል የሚጠራው ጳጳስና ከንግግሩ ማማር የተነሣ አፈወርቅ (Chrysostom) የሚባለውን የቤተ ክርስቲያን መሪ ንጉሡ ስላልፈለገው ወደ አርሜኒያ እንዲሰደድ አድርጎታል። በምዕራቡ ደግሞ የሮሙ አምብሮስ (Ambrose, 339-397) በመባል የሚጠራው ጳጳስ ንጉሡን ቴዎዳሲዎስ በተሰሎንቄ ተፈጽሟል በተባለው የ700 ሰዎች ግድያ ምክንያት ከሥልጣኑ አግልሎ በአደባባይ ንስሐ እስኪገባ ድረስ ቅጣት ወስኖበታል።

እንዲህም ሆኖ፣ በዘመኑ ክልሉ ውስጥ ስመ-ጥር የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ነበሩ። አንደኛው ጀሮም (347-420) ነበር። በአሁኑ ወቅት በተለይም በሮም ካቶሊኮች ዘንድ በስፋት የሚያገለግለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ተርጉሟል። ታማኝ ለመሆን ከመፈለጉ የተነሣም፣ ከብሉይ ኪዳን ወደ ግሪክ ቀድሞ የተተረጎመ ቢሆንም፣ እርሱ ግን በቀጥታ ዕብራይስጡን በመጠቀም ለዘመኑ ሰዎች ቀላሉ ላቲንኛ በሚባለው በላቲኑ ቩልጌት በመተርጎም ለአገልግሎት አብቅቷል።

ጀሮም የዕድሜውን የመጨረሻ 35 ዓመታት በቤተ ልሔም በሚገኝ ገዳም ውስጥ በመሆን ይተረጉምና መጽሐፍ ቅዱስን ያጠናበት ነበር።

ሁለተኛው አውግስቲን (Augustin) ነበር። በሰሜን አፍሪካ በምትገኘው በሂፖ (Hippo) መጋቢ ነበር። የዚህ ሰው አሉታዊ ጐኑ የሮም ካቶሊክን እንደ ብቸኛ የኖኅ መርከብ በመቁጠር፣ በዚያ ውስጥ መገኘት የደኅንነት ተስፋ ነው ማለቱ የሚያስነቅፈው



ሲሆን፣ ጸጋን በተመለከተ ግን የሰው ልጅ በኃጢአት መርከሱን፣ በገዛ ፈቃዱ ራሱን ለዘላለም ሕይወት ማብቃት አለመቻሉን በመግለጽ፣ «ምሕረት የእግዚአብሔር የቸርነት ሕይወት ነው» በማለት ማስተማሩ ደግሞ አስመስግኖታል።

## መሠረታዊ ቁም ነገሮች

1. ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ለክርስትና ዋስ ጠበቃ ነኝ ከማለቱ በፊት የነበሩት 38 ነገሥታት በክርስትና ላይ ስደትን በማስነሣት ይታወቃሉ። ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ በቆየው ስደት ውስጥ ክርስቲያኖች «እያለቁ ይበዙ» ነበር።
2. ክርስትና መሠረታዊ የሕይወት ጥያቄዎችን ከመመለሱ የተነሣ፣ በየጊዜው የሚነሡ ዘመናዊ-መሰል አመለካከቶች ሁሉ የተቃውሞ (የጥላቻ) በትራቸውን ክርስትና ላይ ማድረጋቸው የእምነቱን ሕያውነት ያረጋግጣል።
3. የጋሌሪየስ የመደምደምያ ምስክርነት በሞቱ ለዓት ክርስቲያኖችን አስጠርቶ እንዲጸልዩለት ማድረግ ነበር። ጋሌሪየስ ዲዮክሊሽያኖስን በክርስቲያኖች እንዲጨክን ያደረገ ክፉ ሰው ነበር። የእግዚአብሔር ትዕግሥት ግን በአፍቃሪ ክርስቲያኖች ተገለጠ።
4. ክርስትና ጅምላዊ ገጽታ በኖረው ቁጥር፣ ውጤቱ የክርስቶስን ሥራ ማደብዘዝ ነው። ከዚህም የተነሣ፣ ግላዊ ደኅንነትን ማበረታታት ወሳኝነት አለው። ዲያብሎስ በክርስትና ታሪክ ውስጥ እንክርዳድን በመዝራት የእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ተጽዕኖን የማሳደር ያልተቋረጠ ትግል አለው። መልካሙ ዘር ግን ሁልጊዜ በየትም ስፍራ ክርስቶስን በመግለጥ፣ የለውጥ ምክንያት መሆን ይችላል።

- ቆስጠንጢኖስ በ325 በኒቂያ በተሰበሰበው ጉባኤ ላይ በመገኘቱ የበላይነቱን አስመስክሯል:: የተገኘበት ምክንያት አርዮስ (Arian) በክርስቶስ አምላክነት ላይ የደረሰበትን ጥርጣሬ ለመወሰን ነበር::

- በፓለስቲና ባለችው ቂሣርያ ጳጳስ የነበረው ዩሲቢየስ (263-339)፣ ቆስጠንጢኖስ ጣልቃ ገብ ሆኖ በሚወስዳቸው አርምጃዎቹ ድጋፉን የገለጠ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር::

- ዩሲቢየስ «የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት» በማለት ይጠራል:: እርሱ ሰው፣ «መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በቅንጅት መሥራታቸው ተገቢ ነው» ይላል:: እግዚአብሔር ንጉሡን ክርስቲያን የማድረጉ ምክንያት ሁለት ነው፤ አንዱ፣ ዓለምን በክርስቲያናዊ አሴት በመግዛት ከአረማውያን አምልኮ ነፃ ለማውጣት ሲል ሲሆን፤ ሁለተኛው፣ ክርስትናን በተመለከተ ለቤተ ክርስቲያን ቆስጠንጢኖስ ክርስቶስን በመከተሉ አንድነቷንና ፍቅሯን እንድትጠብቅ ተምሳሌት መሆን ነው፤ በማለት ጽፏል::

- ይህ አመለካከት ለፍቶ በማደግ የሮም መሪዎች የመንግሥቱም፣ የቤተ ክርስቲያንም ዋንኞች እንዲሆኑ አበቃ::

- የቆስጠንጢኖስ ቀጣይ የነበሩት ልጆች ቆንስጣንስ እና ቆንስጣንስ 2ኛ ክርስትናን በማስፋፋት ፈለጉን የተከተሉ ናቸው:: ቆስጠንጢኖስ ምሥራቁን (337-353 ዓ.ም)፣ ምዕራቡን (353-361 ዓ.ም) ገዝቷል::

- በ356 በምዕራቡ ግዛቶች ያሉ የአረማውያን መቅደሶችን አዘጋ፣ የእንስሳ መሥዋዕትን ከለከለ::

- በዚህ ሁሉ «ለጥንቱ ታማኝ ነን» የሚሉ የሮም መሳፍንት አርምጃቸውን ከክህደት በመቁጠር በአረማውያን እምነት የጸኑ ነበሩ፤ አልተነኩም::

- ይህ የክርስትና ጉዳና ግን በ361-363 በነገሠው ዩልያኖስ ከሃዲው ተገለበጠ:: ሰውየው በክርስትና አምነት አድጎ ወደ ሥልጣን በመጣ ጊዜ ፀረ-ክርስቲያን በመሆኑ፣ ከሃዲው ተብሎ ተጠራ::



- ስኒዎፕላቶኒዝም ፍልስፍና ተገዥ ሆነ፣ የእሑድ የአምልኮ ቀንነትን አገደ፣ የትምህርት ሥርዓቱ የአረማውያንን የእምነት ምንነት ገላጭ መሆን አለበት አለ::

- «ተቃውሞ በገሊላውያን» (Against the Galileans) የሚል መጽሐፍን አዘጋጀ:: ይህ ሰው ከፐርሺያውያን ጋር ባደረገው ጦርነት በ363 ተገደለ:: ዩልያኖስ ነፍሱ ከመውጣቷ በፊት ወደ ክርስቶስ እንደ ጸለየ ይነገራል::» «አንተ ገሊላዊው አሸነፍከኝ፣» ብሎ እንደ ሞተ አፈ-ታሪክ ይዘክራል::

ዩልያኖስ ከሃዲውን ተክትሎ ነግሦ የነበረው ቆስጠንጢኖስ የአርዮስን አስተምህሮ ለመቀበል ራሱን አመቻችቶ ለለ ነበር፣ ቤተ ክርስቲያንን ለዳግም ችግር አብቅቷል:: በዚህም ጣልቃ ገብነቱ በርካታ ክርስቲያኖች «ንጉሡ ጫና መፍጠር አይችልም፣» በማለት ተቃወሙ::

- የአሌክሳንድርያው አትናቲዮስ (Athanasius) አርዮስን በመጋፈጥ፤ ንጉሡንም እንደ ሐሰተኛው ክርስቶስ ገልጾ በምንም ዐይነት ሁኔታ ንጉሡ በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ ጣልቃ አይገባም በማለት ሰበከ::

- ንጉሡ አርዮስ የጌታን ራት ይወስድ ዘንድ ጳጳሱ ሆሲንን (Hosius) በ355 አዝዞት ነበር:: ጳጳሱ ግን ለንጉሡ ይህን ምላሽ በድፍረት ሰጠ:-

> «በእግዚአብሔር በሆነው ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ልትገባና ትእዛዝ ልታስተላለፍ አትችልም:: መንግሥትን ለአንተ እግዚአብሔር ሰጥቷል፣ ለእኛ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑን ሰጥቶናል:: ንጉሥ ሆይ፣ ከፉ ኃጢአትን በመሥራት እግዚአብሔርን አትበድል:- «የቄሣርን፣ ለቄሣር፣ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር» (ማቴ. 22:21) ልትሰጥ ይገባሃል:: እኛ መንግሥትህን ለማስተዳደር እንደማንችል፣ አንተም በመቅደስ ተገኝተህ ዕጣን አታጨስም:: ከዚህም የተነሣ፣ ትእዛዝህን አፈጽም ዘንድ አልችልም::»

ይህ አስተሳሰብ ከምሥራቁ የእምነት ፍልስፍና ርቀው ባሉት በምዕራባውያኑ ዘንድ ተግባራዊነቱ በስፋት ሆነ:: የምሥራቁ

